ሃምሌ 3 ቀን 2002 ዓ.ም ጁላይ 10 ቀን 2010 ዓ.ም

# በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን አጠቃላይ ኮሚቴ ስብሰባ ሪፖርት በርን

- ጉባኤው በጸሎት እንዲጀመር ተደረገ።
- ለመረጃነት ይረዳ ዘንድ የሚካሄደው ስብሰባ በቪዲዮ እንዲቀረጽ የተሰብሳቢው ፍቃደኝነት ተጠይቆ በሙሉ ድምጽ ስምምነት ላይ ተደረሰ።
- በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አብይ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ የቀረበው ጽሁፍ ተነበበ።
- በስዊዘርላንድ የሚገኙ ሰበካ ጉባኤያትና ሰንበት ት/ቤቶች በሙሉ የሚተዳደሩበት በሶስቱም አባቶች እንደገና ተዘጋጅቶ የቀረበው ደንብ ተነበበ።
- በተነበበው መተዳደሪያ ደንብ ዙሪያ ከተሰብሳቢዎች ለተነሱ በርካታ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጠ።
- ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በስዊዝ ለሚገኙ ሰበካ ጉባዔያት እንዲሁም ሰንበት ት/ቤቶች መመሪያ እንዲሆን ለአንዲት ቤተክርስቲያናችን ህብረት ታስቦ በተስማሚ ሁኔታ የተዘጋጀ መሆኑን ሰበካ ጉባዔያቸውንና ሰንበት ት/ቤቶችን ወክለው በተገኙ ተውካዮች እንዲሁም በእለቱ በተሰበሰቡት የበርን ምዕመናን ሙሉ ተቀባይነትን አግኝቷል።
- በበርን አቡነ ተክለሃይማኖት ሰበካ ጉባዔ መሃከል ስለተፈጠረው ችግር ውይይት ተካሄደ። በዚህም ላይ በርካታ የተለያዩ ሃሳቦች ከበርን ምዕመናን የተሰጡ ሲሆን በተለይ በበርን አቡነ ተክለሃይማኖት ሰበካ ኮሚቴ ስም እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ድብቅና ከምዕመናኑ ሃሳብና ፍላጎት ውጭ ተለይቶ የተወሰኑ ግለሰቦችን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ እንደሆነ ተወያዮቹ ካነሷቸው ሃሳቦች ለመረዳት ተችሏል። ምንም እንኳን የዛሬውን ስብሰባ የተቃወሙት ውስን የበርን ሰበካ ጉባዔ ኮሚቴ አባላት በዕለቱ ስብሰባ ላይ ባይገኙም ፍላጎታቸውን በቅርበት በተረዱ ምዕመናን አማካይነት ሃሳባቸው ለተሰብሳቢው እንዲደርስ ሆኗል። ከበርን ሰበካ ጉባዔ አባላት መሃከል አብዛኞቹ በዚህ ስብሰባ ላይ የተገኙ ሲሆን አመራሩን የያዙት ውስን አካሎች ግን ቤተክርስቲያኒቱ የግላቸው እንደሆነችና በራሳቸው መንገድ ሊመሩዋት በመፈለጋቸው ምክንያት ከፍተኛ ልዩነት መፍጠራቸው ታውቋል። በማያያዝም በበርን ሰበካ ጉባኤ ስም በጁላይ 3 ቀን 2010 ዓ.ም አስቸኳይ ስብሰባ ተደርጎ ተላለፈ የተባለው ውሳኔ ምልዓተ ጉባኤ ሳይገኝ የተከናወነ ስለመሆኑ በማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚህም ምክንያት በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አጠቃላይ ኮሚቴና የበርን ምዕመናን የተላለፈውን ውሳኔ በምንም አይነት መመዘኛ ሊቀበሉት እንደማችሉ በአጽንኦት ገልጸዋል። በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አብይ ኮሚቴም በተሰብሳቢዎች የተወሰነውን ውሳኔ ተቀብሎ በበርን ሰበካ ጉባዔ ስም ለበርን አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ይሆናል ተብሎ የተነደፈውን መተዳደሪያ ደንብ እንደማይቀበለው ይፋ አድርጓል። አብይ ኮሚቴው በማያያዝም በበርን በኩል ለሚታየው አለመግባባት የበርን ምዕመናን ከሃይማኖት አባቶች ጋር ሆነው በግልጽነት እንዲወያዩ በማሰብ አጠቃላይ ኮሚቴው ከስብሰባው አዳራሽ ወጥቷል።

- የበርን ምዕመናን ከአባቶች ጋር በመሆን በአጥቢያቸው የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት ያመቻቸው ዘንድ በስፋት ከተወያዩ በኋላ በዕለቱ በስብሰባው ከተገኙት መሃከልና ቀድሞ በሰበካ ኮሚቴነት ካገለገሉት ውስጥ ወይዘሪት እምነት ታደሰን ጨምሮ በድምሩ አምስት የጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን መርጧል።
- የስራ ድርሻቸውም

1. በበርን የሚካሄደው መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲቀጥል ማስተባበር፣
2. በበርን የሚታየውን የውስጥ ችግር በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት እንዲያገኝ መጣር፣
3. በስዊዘርላንድ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አብይ ኮሚቴ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በማድረግ ስለ አንዲት ቤተክርስቲያናችን በጋራ መንቀሳቀስ።

ለበርን አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን በጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴነት የተመረጡት ተመራጮች ስም ዝርዝር እንደሚከተለው ነው።

1. ወይዘሪት እምነት ታደሰ
2. ወይዘሪት ትደነቅ ግርማ
3. ወይዘሮ ፋሲካ ግዛው
4. ወይዘሮ ሜላት ሽመልስ
5. ወይዘሮ ኤልሳ በላይ

- በመጨረሻም የበርን ምዕመናን የደረሱበትን ውሳኔ በመቀበል የእለቱ መርሃ ግብር በጸሎት ተፈጽሟል።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር



ዶ/ር መርዕድ ታየ
በስዊዘርላንድ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ጠቅላላ ኮሚቴ ሰብሳቢ



ተስፉ ወልደስላሴ
በስዊዘርላንድ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ጠቅላላ ኮሚቴ ጸሃፊ

ግልባጭ
ለካህናት
ለበርን ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ
ለጄኔቫ ጸሃዩ ጽድቅ መድሃኔዓለም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ
ለዙሪክ ደብረገነት ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ
ለሎዛን ደብረሃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ

Petruskirche und Kirchgemeindehaus
Brunnadernstr. 40
3006 Bern
Kirchgemeinde Evangelisch-reformierte Gesamtkirchgemeinde Bern Nydegg
Gemeindehaus Burgfeld
Burgdorfholzstrasse 35
3006 Bern, Schweiz